የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሀያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፰
አዲስ አበባ መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 28
ADDIS ABABA 2nd Day of April, 2020.

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

የኢንቨስትመንት አዋጅ …………………………ገጽ ፲፪ሺ፫፻፹፫

**Content**

Proclamation No. 1180/2020

Investment Proclamation ............................Page 12383

lawyer.et

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹/፪ሺ፲፪**

**የኢንቨስትመንት አዋጅ**

አምራች እና አስቻይ የኢንቨስትመንት መስኮችን ጨምሮ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ በማበረታታት እና በማስፋፋት የአገሪቱን የኢኮኖሚ ልማት ማፋጠን፣ የእድገቱን ዘላቂነት ማረጋገጥ፣ የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማጠናከር እና የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

የአገራዊ ኢኮኖሚውን ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪነት የሚያፋጥን፣ የወጪ ንግድን የሚያስፋፋ፣ ሰፊ እና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል የሚፈጥር፣ እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች መካከል ዘላቂ እና ተመጋጋቢ ትስስርን የሚያሳልጥ የኢኮኖሚ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

**PROCLAMATION NO. 1180/2020**

**INVESTMENT PROCLAMATION**

**RECOGNIZING** that increasing the role of private sector investment in all sectors of the economy including in productive and enabling sectors has become necessary to accelerate the economic development of the country, ensure its sustainability, strengthen domestic production capacity and thereby improve the living standards of its people;

**WHEREAS** it has become necessary to create an economic framework that fast-tracks the global competitiveness of the National economy, increases export performance, generates more and better employment opportunities, and facilitates sustainable and entwined linkage among various economic sectors;

ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የውጭ ባለሀብቶች ኢንቨስትመንት መጠን እና የተሳትፎ መስክ በማስፋት የዕውቀት፣ የክህሎት፣ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እና ስርጸትን ማፋጠን ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ትስስርን ማስፋት፣ የኢንቨስትመንት ክልላዊ ስርጭትን ማሻሻል፣ እንዲሁም የውጭ ካፒታል በመጠቀም የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን ተወዳዳሪነት ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፤

ኢንቨስትመንቶች በአገራዊ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች የተመለከቱ ግቦችን ማሳካታቸውን እንዲሁም በሕግ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር እና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢንቨስትመንት ፍሰት፣ መስፋፋት፣ እና ቆይታን ማሳደግ እንዲቻል ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ይበልጥ ግልጽ፣ ተገማች፣ እና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**WHEREAS** it has become necessary to further increase and diversify foreign investment inflow to accelerate inward transfer and diffusion of knowledge, skill, and technology;

**RECOGNIZING** that it has become necessary to maximize linkages between foreign and domestic investments, promote equitable distribution of investments among regions, and leverage foreign capital to promote the competitiveness of domestic investors;

**RECOGNIZING** that it has become essential to put in place a system of monitoring and supervision to ensure that investments deliver on promised potentials stated in National Investment Objectives and are operated in accordance with the law;

**WHEREAS** the investment administration system has to be transparent, predictable, and efficient to increase investment attraction, retention, and expansion;

**WHEREAS,** to these ends, it has become necessary to revise the existing law on investment;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

lawyer.et

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፲፩፻፹/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፡-

፩/ **"ኢንቨስትመንት"** ማለት አዲስ ድርጅትን ለማቋቋም፣ ወይም ነባር ድርጅትን ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፤

፪/ **"ድርጅት"** ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

፫/ **"ካፒታል"** ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንጻ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአእምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ የንግድ ሀብት ነው፤

፬/ **"ባለሀብት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤

፭/ **"የአገር ውስጥ ባለሀብት"** ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ፤

ሀ) ኢትዮጵያዊ ዜጋ፤

ለ) ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያዊ ዜጋ የተያዘ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፤

ሐ) መንግሥት፤

መ) የመንግሥት የልማት ድርጅት፤

## PART ONE

## GENERAL

**1.Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Investment Proclamation No1180/2020".

**2. Definitions**

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **"Investment"** means expenditure of capital in cash or in kind or in both by an investor to establish a new enterprise, or to acquire, in whole or in part, or to expand or upgrade an existing enterprise;

2/ **"Enterprise"** means an undertaking established for profit-making;

3/ **"Capital"** means local or foreign currency, negotiable instrument, machinery or equipment, building, working capital, property right, intellectual property right, or other tangible or intangible business assets;

4/ **"Investor"** means a Domestic or Foreign investor who has invested capital in Ethiopia;

5/ **"Domestic Investor"** means any one of the following who has invested capital in Ethiopia:

a) An Ethiopian National;

b) An Enterprise incorporated in Ethiopia and wholly owned by Ethiopian National;

c) The Government;

d) a Public Enterprise;

lawyer.et

ሠ) አግባብነት ባለው ሕግ የተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበር፤

ረ) አግባብነት ባለው ሕግ ወይም ኢትዮጵያ ባጸደቀችው ዓለምአቀፍ ስምምነት መሠረት እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፤

ሰ) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ-አንቀጽ ፭ ፊደል ተራ (ሀ) እስከ ረ) በተመለከቱት በማናቸውም መካከል በጋራ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋመ ድርጅት፤

ሸ) ይህ አዋጅ ሲወጣ በሥራ ላይ የነበረ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ብቻ ሆኖ ከዚህ በፊት ታውጀው ከጊዜ በኋላ በተሻሩ ሕጎች መሠረት የአገር ውስጥ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጠው እና አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ በሥራ ላይ ያለ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት፤ ወይም

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (ሸ) የተገለጸ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ ብቻ ሆኖ በዚሁ ንዑስ-አንቀጽ የተመለከተ የውጭ አገር ዜጋ ተወላጅ ነው፤

፮/ **"የውጭ ባለሀብት"** ማለት የውጭ ካፒታል ወደ ኢትዮጵያ በማስገባት ሥራ ላይ ያዋለ፤

ሀ) የውጭ አገር ዜጋ፤

ለ) የውጭ አገር ዜጋ በባለቤትነት የተሳተፈበት ድርጅት፤

ሐ) በማንኛውም ባለሀብት ውጭ አገር የተቋቋመ ድርጅት፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፮) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) ወይም (ሐ) በተመለከቱት ማናቸውም ባለሀብቶች መካከል በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፣ ወይም፤

ሠ) እንደ ውጭ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊ ነው፤

e) A cooperative society established as per the relevant law;

f) A Foreign National or Foreign Enterprise treated as domestic investor as per the relevant law or international treaty ratified by Ethiopia;

g) An Enterprise incorporated in Ethiopia jointly between any of the investors specified under Sub-article (5) paragraphs (a) to (f) of this Article;

h) A Foreign National or Foreign Enterprise accorded a domestic investor investment permit as per laws which were in effect when the permit was issued but which have since been repealed and continues to operate in Ethiopia, provided that this applies only in respect of investments that are operational at the time of enactment of this Proclamation;

i) Descendant of a foreign national specified under Sub-article (5) paragraph (h) of this Article, provided that this applies only in respect of investments specified in the same Sub-article;

6/ **"Foreign Investor"** means any one of the following who has invested foreign capital in Ethiopia:

a) A Foreign National;

b) An Enterprise in which a Foreign National has an ownership stake;

c) An Enterprise incorporated outside of Ethiopia by any investor;

d) An Enterprise established jointly by any of the investors specified under Sub-article (6) paragraphs (a), (b) or (c) of this Article; or

e) An Ethiopian permanently residing abroad and preferring treatment as a Foreign investor;

lawyer.et

፯/ **"የመንግሥት የልማት ድርጅት"** ማለት ሙሉ በሙሉ በመንግሥት ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ነው፤

፰/ **"ማስፋፋት" ወይም "ማሻሻል"** ማለት ሊደረስበት የሚችል የነባር ድርጅትን የማምረት ወይም አገልግሎት የመስጠት አቅም ቢያንስ ሀምሳ በመቶ በመጠን በማሳደግ ወይም የነባር ድርጅትን አዲስ የማምረቻ ወይም አገልግሎት መስጫ መስመር በመጨመር ምርትን ወይም አገልግሎትን ቢያንስ መቶ በመቶ በዓይነት ማሳደግ ወይም በሁለቱም ማሳደግን ያጠቃልላል፤

፱/ **"የቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት ምርትን ለማምረት ወይም የአመራረት ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለማሻሻል ወይም አገልግሎትን ለመስጠት የሚረዳ ሥርዓት ያለው ዕውቀት ማስተላለፍ ሲሆን የሥራ አመራር እና የቴክኒክ ዕውቀት እንዲሁም የግብይት ሁኔታ ቴክኖሎጂንም ይጨምራል፣ ሆኖም ዕቃዎችን ብቻ ለመሸጥ ወይም ለማከራየት የሚደረግን ግንኙነት አይሸፍንም፤

፲/ **"ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳይኖረው የሚያደርገው ትብብር"** ማለት መቶ በመቶ ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገው የውል ግንኙነት ሆኖ የውጭ ድርጅቱ ለአገር ውስጥ ባለሀብቱ በሙሉ ወይም በከፊል የሚሰጠው የሚከተሉት ትብብሮችን ይጨምራል፤

ሀ) አስተማማኝ የውጭ ገበያ ግኝት፣

ለ) ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን የማምረት ዘዴ፣

ሐ) የውጪ ንግድ ሥራ አመራር ዕውቀት፣

መ) በውጭ ገበያ የመሸጥ ስልት፣

ሠ) ለውጪ ምርት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎች እና ግብዓቶች አቅርቦት ስልት፣

7/ "**Public Enterprise**" means an enterprise wholly owned by the government;

8/ **"Expansion" or "Upgrading"** means increasing in volume, by at least 50 percent of the attainable production or service rendering capacity of an existing enterprise, or increasing in variety by at least 100 percent by introducing new production or service rendering line of an existing enterprise, or increment by both;

9/ **"Transfer of Technology"** means the transfer of systematic knowledge for the manufacture of a product, the application or improvement of a process or for rendering service, including management and technical know-how as well as marketing technologies, but may not extend to transactions involving mere sale or lease of goods;

10/ **"Export-Oriented Non-equity Based Foreign Enterprise Collaboration"** means a hundred percent export-oriented contractual agreement between a domestic investor and foreign enterprise in which the foreign enterprise provides, among others, all or some of the following:

a) Guaranteed external market access;
b) Production know-how of products for export market;
c) Export business management know-how;
d) Export marketing know-how;
e) Strategies for the supply of raw materials and intermediate inputs needed for export products;

lawyer.et

፲፩/ **"መንግሥት"** ማለት የፌደራሉ መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድር ነው፤

፲፪/ **"ክልል"** ወይም "የክልል መስተዳድር" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፲፫/ **"ቦርድ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤

፲፬/ **"ኮሚሽን"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፭ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤

፲፭/ **"ጉባዔ"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፬ መሠረት የተቋቋመ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳደሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ ነው፤

፲፮/ **"አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት"** ማለት ኮሚሽኑ፣ ከኮሚሽኑ በውክልና ሥልጣን የተሰጠው የፌደራል መንግሥት አካል፣ ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ወይም ኢንቨስትመንት ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው የክልል መስተዳድር አካል ነው፤

፲፯/ **"የኢንዱስትሪ ፓርክ"** የሚለው ሐረግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች አዋጅ ቁጥር ፰፻፹፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፪/፩/ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል ፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ይጨምራል።

11/ **"Government"** means the Federal Government or a Regional State Administration;

12/ **"Region" or "Regional State Administration"** means any Regional State specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa City Administration and Dire Dawa City Administration;

13/ **"Board"** means the Ethiopian Investment Board reestablished under Article 30 of this Proclamation;

14/ **"Commission"** means the Ethiopian Investment Commission reestablished under Article 35 of this Proclamation;

15/ **"Council"** means the Federal Government and Regional State Administrations Investment Council established under Article 44 of this Proclamation;

16/ **"Appropriate Investment Organ"** means the Commission, a federal government body carrying out functions delegated by the Commission, or the relevant regional state administration body authorized to issue investment permits or administer investments;

17/ **"Industrial Park"** shall have the meaning assigned to it under Article 2/1/ of the Industrial Parks Proclamation No. 886/2015;

18/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

lawyer.et

፫. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በማዕድን እና በነዳጅ ፍለጋ፣ ምርመራ እና የማምረት ሥራዎች ላይ ከሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች በስተቀር በሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፬. **የሥልጣን ክልል**

፩/ የሚከተሉት ኢንቨስትመንቶች አስተዳደር በኮሚሽኑ የሥልጣን ክልል ሥር ይወድቃሉ፦

ሀ) ሙሉ በሙሉ በውጭ ባለሀብት የተያዘ ኢንቨስትመንት፤

ለ) በአገር ውስጥ እና በውጭ ባለሀብቶች በጋራ የተያዘ ኢንቨስትመንት፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ-አንቀጽ (፭) ከፊደል ተራ (ረ) እስከ (ቀ) በተደነገገው መሠረት እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት በተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ባልሆነ የውጭ አገር ዜጋ የሚካሄድ ኢንቨስትመንት፤ እና

መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የኢንቨስትመንት መስክ አግባብ ካለው የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣት ባለበት የአገር ውስጥ ባለሀብት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት ወይም ማስተላለፍ ወይም ማሰራጨት አገልግሎት፣ እና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሥራዎች ላይ ለሚሰማራ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት፣ የማደስ፣ የማሻሻል፣ የመለወጥ፣ የመተካት፣ የመሰረዝ እና የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ወይም ማሻሻያ ፈቃድ የመስጠት ሥራን እንደ ቅደም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ኮሚሽኑን በመወከል ያከናውናሉ።

3. **Scope of Application**

This Proclamation shall apply to all investments carried out in Ethiopia except to investments in the prospecting, exploration and development of minerals and petroleum.

4. **Jurisdiction**

1/ The administration of the following investments shall be under the jurisdiction of the Commission:

a) Wholly foreign owned investment;

b) Joint investment made by domestic and foreign investors;

c) Investment made by a foreign national, not Ethiopian by origin, who is treated as a domestic investor pursuant to Article 2(5) paragraphs (f) to (i) of this Proclamation; and

d) Investment made in areas eligible for incentives by a domestic investor who is required to obtain a business license from an appropriate Federal Body.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-article (1) of this Article, the issuance, renewal, amendment, substitution, replacement and cancellation of investment permits, and the issuance of investment expansion or upgrading permits for air transport services, the generation or transmission or distribution of electric power, and the provision of communications services shall be carried out by the Ethiopian Civil Aviation Authority, the Ethiopian Energy Authority, and the Ethiopian Communications Authority, respectively, representing the Commission.

lawyer.et

፫/ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን፡-

ሀ) በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት የሰጧቸውን አገልግሎቶች የሚመለከት ሪፖርት በየሦስት ወር ለኮሚሽኑ ያቀርባሉ፤

ለ) የየዘርፎቹን እምቅ አቅም ለመለየት የሚያስፈልጉ ጥናቶችን የማካሄድ፣ ዘርፍ-ተኮር የኢንቨስትመንት ልማት ስትራቴጂዎችን የመቅረጽ እና የኢንቨስትመንት እድሎችን የማስተዋወቅ ሥራዎችን ከኮሚሽኑ ጋር በመቀናጀት ያከናውናሉ።

፬/ የክልሎች አግባብ ያላቸው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉ ኢንቨስትመንቶችን የማስተዳደር ሥልጣን ይኖራቸዋል።

## ክፍል ሁለት
## የኢንቨስትመንት ዓላማዎች

### ፭.የኢንቨስትመንት ዓላማዎች

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የኢንቨስትመንት ዓላማ ፈጣን፣ አካታች እና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ልማት እንዲኖር በማድረግ የኢትዮጵያን ህዝቦች የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ሆኖ የሚከተሉትን ዝርዝሮች ይጨምራል፡-

፩/ በልዩ የአምራች እና አስቻይ የልማት ዘርፎች ኢንቨስትመንትን በማሳደግ ብሔራዊ የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነትን ማጠናከር፤

፪/ ለኢትዮጵያውያን ሰፊ እና ጥራት ያለው የሥራ ዕድል መፍጠር እና ለአገሪቱ ዕድገት የሚያስፈልገውን የዕውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ማሳለጥ፤

3/ The Ethiopian Civil Aviation Authority, the Ethiopian Energy Authority, and the Ethiopian Communications Authority shall:

a) Submit to the Commission a quarterly report regarding services they rendered through their Delegated Powers;

b) Coordinate with the Commission to undertake studies identifying sectoral potentials, and sector specific investment development strategies, and engage in investment promotion works.

4/ Appropriate investment Organs of Regions shall have jurisdiction to administer investments other than those specified under Sub-articles (1) and (2) of this Article.

## PART TWO
## INVESTMENT OBJECTIVES

### 5. Investment Objectives

The investment objective of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is to improve the living standard of the peoples of Ethiopia by realizing a rapid, inclusive and sustainable economic and social development. The particulars of the objective include the following:

1/ To enhance the competitiveness of the national economy by promoting investments in productive and enabling sectors;

2/ To create more and better employment opportunity for Ethiopians and advance the transfer of knowledge, skills and technology required for the development of the country;

lawyer.et

፫/ ውጭ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን በመጠን፣ በዓይነት እና በጥራት እንዲጨምሩ በማበረታታት የውጭ ምንዛሪ ግኝትን ማሳደግ፤

፬/ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪን ማዳን፤

፭/ በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት የግል ሴክተሩን ሚና ማሳደግ፤

፮/ የአገሪቱን የተፈጥሮ፣ የባህል እና ሌሎች ሀብቶች ጥቅም ላይ ማዋል እና ማልማት፤

፯/ በተለያዩ ዘርፎች እንዲሁም በውጭ እና የአገር ውስጥ ኢንቨስትመንቶች መካከል ያለውን ትስስር በማጠናከር የተቀናጀ ኢኮኖሚ መፍጠር፤

፰/ የማህበራዊ እና የአካባቢ ጥበቃ እሴቶችን የሚከተሉ እና አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያላቸው ኢንቨስትመንቶችን ማበረታታት።

## ክፍል ሦስት
## የኢንቨስትመንት መስኮች፣ የድርጅት ዓይነቶች እና የካፒታል መጠን

### ፮. የኢንቨስትመንት መስኮች

፩/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለሀብት ለሕግ፣ ለሞራል፣ ለማህበረሰብ ጤና ወይም ደህንነት ተጻራሪ ካልሆነ በስተቀር በማናቸውም የኢንቨስትመንት መስክ መሰማራት ይችላል።

፪/ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ፣ ለአገር ውስጥ ባለሀብቶች የተከለሉ፣ እና ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በቅንጅት የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ዝርዝር በደንብ ይወሰናል።

3/ To increase foreign exchange earnings by encouraging the expansion in volume, variety and quality of the country's export products and services;

4/ To save foreign exchange through local production of import substitutes;

5/ To augment the role of the private sector in the country's economic development;

6/ To exploit and develop natural, cultural, and other resources of the country;

7/ To create an integrated economy by strengthening inter-sectoral and foreign-domestic investment linkages;

8/ To encourage socially and environmentally responsible investments.

## PART THREE
## AREAS OF INVESTMENT, FORMS OF ENTERPRISE AND CAPITAL REQUIREMENTS

### 6. Areas of Investment

1/ Subject to the provisions of this Article, any investor may engage in any area of investment except where it is contrary to law, moral, public health or security.

2/ Areas of investment reserved for joint investment with the Government, for domestic investors, and for joint investment with domestic investors shall be specified by Regulation.

lawyer.et

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት ከሚከለሉ በስተቀር ሁሉም የኢንቨስትመንት መስኮች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት ይሆናሉ።

፬/ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፪) እና (፫) መሠረት የሚወሰኑ የኢንቨስትመንት መስኮችን ዝርዝር ሊያሻሽል ይችላል።

**፯.ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት**

እንደ አግባብነቱ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታ እና አስተዳደር ኤጀንሲ ወይም በመንግሥት እና የግል ዘርፍ አጋርነት የሚቋቋሙ ፕሮጀክቶችን ለማስፈጸም በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ተቋም፤ ማንኛውም የግል ባለሀብት ከመንግሥት ጋር በቅንጅት በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት የሚያቀርበውን የፕሮጀክት ሀሳብ ይቀበላል፣ ተገቢነት ባለው ሕግ የተመለከቱ የአፈጻጸም ሂደቶችን በመከተልም አቅርቦ ያስወስናል፣ ሲፈቀድም በቅንጅት ተሳታፊ የሚሆነው የልማት ድርጅት እንዲሰየም ወይም የፕሮጀክት ኩባንያ እንዲቋቋም ያደርጋል።

**፰. ኢንቨስትመንት የሚካሄድባቸው ድርጅቶች ዓይነት**

፩/ ኢንቨስትመንት ከሚከተሉት ድርጅቶች በአንደኛው ሊካሄድ ይችላል፦

ሀ) በግለሰብ፤

ለ) ኢትዮጵያ ውስጥ ወይም ውጭ አገር በተቋቋመ ድርጅት፤

ሐ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተቋቋመ የመንግሥት የልማት ድርጅት፤

መ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተቋቋመ የህብረት ሥራ ማህበር።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ላይ በተመለከቱት የድርጅት ዓይነቶች የሚካሄድ ማንኛውም ኢንቨስትመንት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ መሠረት መመዝገብ አለበት።

3/ Except those reserved in accordance with Sub-article (2) of this Article, all areas of investment shall be open to foreign investors.

4/ The Board may revise the list of investment areas specified as per Sub-articles (2) and (3) of this Article as it deems it necessary.

**7. Investments Undertaken Jointly with the Government**

The Public Enterprises Holding and Administration Agency or an authority statutorily mandated to implement projects established by way of public-private-partnership, as appropriate, shall receive investment proposals submitted by any private investor intending to invest jointly with the Government; it shall follow procedures established under the pertinent laws for decision, and, upon approval, designate a Public Enterprise or establish a project company to invest as partner in the joint investment.

**8. Forms of Enterprise for Carrying out Investments**

1/ Investments may be carried out in one of the following Enterprises:

a) Sole proprietorship;

b) Enterprise established in Ethiopia or abroad;

c) Public Enterprise established in accordance with the relevant law;

d) Cooperative society formed in accordance with the relevant law.

2/ Any investment made in the forms prescribed under Sub-article (1) of this Article shall be registered in accordance with the Commercial Code of Ethiopia or other applicable law.

lawyer.et

፫/ ማንኛውም ውጭ አገር ተቋቁሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ ድርጅት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እና ድርጅቶችን በሚመለከቱ ሌሎች ሕጎች ይገዛል።

**፱. <u>ከውጭ ባለሀብት የሚጠየቅ ዝቅተኛ የካፒታል መጠን</u>**

፩/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት በዚህ አዋጅ መሠረት በኢንቨስትመንት መስክ ለመሰማራት ለአንድ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከ ፪፻ሺ (ሁለት መቶ ሺ.ህ) የአሜሪካን ዶላር ያላነሰ ካፒታል መመደብ አለበት።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት በኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማራ የውጭ ባለሀብት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን ፩፻፶ሺ(አንድ መቶ ሀምሳ ሺ.ህ) የአሜሪካን ዶላር ይሆናል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በአርክቴክቸር ወይም በኢንጂነሪንግ ሥራዎች ወይም በተዛማጅ የቴክኒክ ማማከር አገልግሎት፣ በቴክኒክ ምርመራ እና ትንተና ወይም በአሳታሚነት ሥራ የሚሰማራ የውጭ ባለሀብት የሚጠየቀው ዝቅተኛ የካፒታል መጠን፦

ሀ) በተናጠል ሲሆን ፻ሺ (አንድ መቶ ሺ) አሜሪካን ዶላር፣

ለ) ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ሲሆን ፶ሺ (ሀምሳ ሺ) አሜሪካን ዶላር ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ዝቅተኛ የመነሻ ካፒታል የመመደብ ግዴታ በሚከተሉት ባለሀብቶች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፤

ሀ) ከነባር ኢንቨስትመንቱ የሚያገኘውን ትርፍ ወይም የትርፍ ድርሻ በማንኛውም ለውጭ ባለሀብት በተፈቀደ መስክ መልሶ ሥራ ላይ የሚያውል የውጭ ባለሀብት፤



3/ Any enterprise registered in Ethiopia having been established abroad shall be governed by the Commercial Code of Ethiopia and other laws applicable to enterprises.

**9. <u>Minimum Capital Requirements for Foreign Investors</u>**

1/ Any foreign investor, to be allowed to invest under this Proclamation, shall be required to allocate a minimum capital of USD 200,000.00 (two hundred thousand) for a single investment project.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, the minimum capital required of a foreign investor jointly investing with a domestic investor shall be USD 150,000.00 (one hundred fifty thousand).

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, the minimum capital required of a foreign investor investing in architectural or engineering works or related technical consultancy services, technical testing and analysis or in publishing works shall be:

a) USD 100,000.00 (one hundred thousand) if the investment is made on his own;

b) USD 50,000.00 (fifty thousand) if the investment is made jointly with a domestic investor.

4/ The minimum capital requirement under this Article shall not apply to:

a) Foreign investor re-investing his profits or dividends generated from his existing enterprise in any investment area open for foreign investors;

lawyer.et

ለ) ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ወደ አክስዮን ማኅበር ሲለወጥ ለአክስዮን ማኅበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባልነት የሚመረጡ ግለሰቦች፤ እና

ሐ) የውጭ ባለሀብት ሙሉ ድርጅትን ወይንም በድርጅቱ ያለውን አክሲዮን በሙሉም ሆነ በከፊል የሚገዛ የውጭ ባለሀብት።

፭/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ወደ አገር ውስጥ ያስገባውን የኢንቨስትመንት ካፒታል በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በማስመዝገብ የምስክር ወረቀት መያዝ ይኖርበታል። አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ለባለሀብቱ የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት ቅጂ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይልካል።

## ክፍል አራት
## የኢንቨስትመንት ፈቃድ

### ፲.የኢንቨስትመንት ፈቃድ አስፈላጊነት እና አሰጣጥ

፩/ የሚከተሉት ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል፦

ሀ) የውጭ ባለሀብቶች፤

ለ) በቅንጅት በኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ-አንቀጽ (፭) ፊደል ተራ (ረ)፣ (ሰ)፣ (ሸ) እና (ቀ) የተመለከቱ እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት በመቆጠር በኢንቨስትመንት የሚሰማሩ ባለሀብቶች፤

መ) የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በሚሰጥበት የኢንቨስትመንት መስክ የሚሰማሩ እና የማበረታቻው ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች፤ እና



b) Persons elected as members of board of directors following the change of a private limited company to share company; and

c) A foreign investor buying the entirety of an existing enterprise owned by a foreign investor or the shares therein.

5/ Any foreign investor bringing investment capital into the country shall have such capital registered by the appropriate investment organ with in one year and obtain a certificate of registration. The appropriate investment organ shall send a copy of the certificate to the National Bank of Ethiopia.

## PART FOUR
## INVESTMENT PERMIT

### 10. Requirement and Issuance of Investment Permit

1/ The following investors shall be required to obtain investment permits:

a) Foreign investors;

b) Domestic and foreign investors investing jointly;

c) Investors investing as domestic investors pursuant to Article 2 Sub-article (5) paragraphs (f), (g), (h) and (i) of this Proclamation;

c) Domestic investors who, investing in areas eligible for incentives, seek to be beneficiaries of such incentives; and

lawyer.et

ሠ) የማስፋፊያ ወይም የማሻሻያ ኢንቨስትመንት ማካሄድ የሚፈልግ ባለሀብት ሆኖ ኢንቨስትመንቱ ማበረታቻ በሚሰጥበት መስክ ውስጥ የሚወድቅ ከሆነ እና ባለሀብቱ በማበረታቻው ተጠቃሚ ለመሆን ከመረጠ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሐ) ድንጋጌ ቢኖርም እንደ የአገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ በማይሰጠው፣ ወይም ማበረታቻ የሚሰጠው ቢሆንም ማበረታቻ የማግኘት መብቱን በመተው ያለኢንቨስትመንት ፈቃድ ኢንቨስትመንት ላይ ሊሰማራ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ ነባር ድርጅት ገዝቶ ባለበት ሁኔታ ለማካሄድ ወይም የነባር ድርጅትን አክስዮን ለመግዛት የሚፈልግ የውጭ ባለሀብት ጥያቄውን ለኮሚሽኑ በማቅረብ በቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል። ኮሚሽኑ የተጠየቀውን ፈቃድ ያለበቂ ምክያት ሊከለክል ወይም ሊያዘገይ አይችልም።

፬/ ማንኛውም ባለሀብት በማናቸውም ጊዜ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃዶችን በአንድ ላይ ሊይዝ አይችልም።

**፲፩. <u>የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት</u>**

፩/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ባለሀብቱ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለገበያ ማቅረብ እስከሚጀምርበት ጊዜ ድረስ በየአመቱ መታደስ አለበት። የንግድ ሥራ ፈቃድ ከወጣ በኋላ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መታደስ አይኖርበትም፡፡

፪/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሳት ጥያቄ ፈቃዱ የሚያገለግልበት የአንድ አመት ጊዜ ባለቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።

e) An investor seeking to expand or upgrade an existing investment, provided that the investment is eligible for incentives and the investor seeks to be beneficiary of such incentives.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) paragraph (c) of this Article, a foreign national of Ethiopian origin treated as a domestic investor shall have the right to invest without acquiring investment permit in areas not eligible for incentives, or, in areas eligible for incentives, by waiving his right to claim incentives.

3/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, a foreign investor seeking to buy an existing enterprise in order to operate it in its current state or to buy shares of an existing enterprise shall obtain prior approval from the Commission. The Commission shall not deny or delay the approval sought without sufficient cause.

4/ No investor may, at any time, hold domestic and foreign investor permits simultaneously.

**11. <u>Renewal of Investment Permit</u>**

1/ An investment permit shall be renewed annually until the investor commences marketing his products or services. There shall be no need for renewal of investment permit after issuance of business license.

2/ An application for renewal of investment permit shall be submitted within one month after the end of a period of one year for which the permit was valid.

lawyer.et

፫/ ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ትግበራ ሳይጀምር ሁለት ዓመት ካለፈው ወይም የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ትግበራውን ለማጠናቀቅ አግባብ ካለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ጋር ከሚስማማበት ጊዜ በሁለት ዓመት ከዘገየ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይሰረዛል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ባለሀብቱ የፕሮጀክት ትግበራውን ሊጀምር ወይም ሊያጠናቅቅ ያልቻለው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካመነበት ፈቃዱ ይታደሳል።

## ፲፪. በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ማስተላለፍ

የንግድ ሥራ ፈቃድ ከማውጣቱ በፊት በትግበራ ላይ የሚገኝ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ለሌላ ባለሀብት ማስተላለፍ የሚፈልግ ማንኛውም ባለሀብት ጥያቄውን አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በማቅረብ ማስፈቀድ ይኖርበታል። አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የተጠየቀውን ፈቃድ ያለበቂ ምክንያት ሊከለክል ወይም ሊያዘገይ አይችልም። ለዚህ ድንጋጌ አፈፃፀም የሚስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

## ፲፫. የኢንቨስትመንት ፈቃድን ማገድ ወይም መሰረዝ

፩/ማንኛውም ባለሀብት፡-

ሀ) አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠይቀውን መረጃ ወይም የፕሮጀክት አፈጻጸም ሪፖርት በትክክል እና በወቅቱ ካላቀረበ፣ ወይም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት የተሳሳተ ሪፖርት ካቀረበ፤

3/ An investment permit shall be revoked if an investor fails to commence implementation of his project within two years of being issued the permit or has delayed the completion of the project by two years from the time that will be agreed with the appropriate investment organ.

4/ Notwithstanding the provision of Sub-article (3) of this Article, the appropriate investment organ may renew the investment permit if it is convinced of the existence of sufficient cause prompting delay in the commencement or completion of the project.

## 12. Transfer of Investment Project Under Implementation

Any investor wishing to transfer to another investor a project which is in implementation phase and for which no business license has been issued shall submit his request to the appropriate investment organ and obtain the approval such organ. The appropriate investment organ shall not deny or delay the approval sought without sufficient cause. The detailed conditions nessary to foe the implementation of this provisions shall be specified by a Directive to be enacted by a Commission.

## 13. Suspension or Revocation of Investment Permit

1/ The investment permit of an investor shall be suspended if the investor:

a) Fails to submit accurate and timely information or project implementation report requested by the appropriate investment organ pursuant to this Proclamation, or intentionally or negligently presents incorrect report;

lawyer.et

ለ) የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ወይም የፈቃድ እድሳትን ያገኘው በማታለል ወይም የሐሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ፤

ሐ) የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከተሰጠበት ዓላማ ውጭ ከተገለገለበት፤

መ) ያለበቂ ምክንያት በአዋጁ እና በአዋጁ መሠረት በወጡ ደንቦች ላይ በተመለከተው መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ካላሳደሰ፤

ሠ) የፕሮጀክት ትግበራ ጀምሮ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ-አንቀጽ (፫) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ካላጠናቀቀ እና ፕሮጀክቱን ሊያጠናቅቅ እንደማይችልም ከታመነ፤ ወይም

ረ) ይህን አዋጅ፣ በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ድንጋጌዎችን ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች ከተላለፈ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይታገዳል።

፪/ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የታገደበት ባለሀብት ለዕገዳው ምክንያት የሆነውን ጉዳይ እንዲያስተካክል የአንድ ዓመት ጊዜ ይሰጠዋል።

፫/ ማንኛውም ባለሀብት፡-

ሀ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ-አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ-አንቀጽ (፫) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ የኢንቨስትመንት ትግበራ ካልጀመረ፤

ለ) ለኢንቨስትመንት ፈቃዱ እገዳ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካላስተካከለ፤

ሐ) የኢንቨስትመንት ሥራውን በፈቃዱ ከተወ፤ ወይም

መ) ተፈጻሚነት ባለው ሕግ መሠረት የተሰጡትን ማበረታቻዎች ከታቀደላቸው ዓላማ ውጭ ካዋለ ወይም ከሕግ ውጭ ለሌላ ሰው ካስተላለፈ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ ይሰረዛል።

b) Obtains the investment permit or secures its renewal fraudulently or by submitting a false information or statement;

c) Uses the investment permit incompatibly with the objective for which it was issued;

d) Fails, without good cause, to renew the permit in accordance with the requirements specified in this Proclamation and regulations issued hereunder;

e) Commences project implementation but fails to complete same within the time limit provided under Article 11 Sub-article (3) of this Proclamation and where it is believed that the project will not be completed at all; or

f) Violates the provisions of this Proclamation, or Regulations and Directives issued to implement this Proclamation, or other pertinent Laws.

2/ An investor whose permit is suspended shall be given one year to take corrective measures.

3/ The investment permit of an investor shall be revoked if the investor:

a) Subject to the provision of Article 11 Sub-article (4) of this Proclamation, fails to commence investment project implementation as per Article 11 Sub-article (3) of same;

b) Fails to rectify the issue that caused the suspension of the investment permit within the time given to him;

c) Voluntarily forsakes his investment activity; or

d) Misuses or illegally transfers to a third-party investment incentives granted pursuant to the Pertinent Laws;

lawyer.et

፬/ አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወስደውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመሰረዝ እርምጃ ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ያሳውቃል። የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰረዘበት ባለሀብት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ሲያገኝ የነበረው ጥቅም ወዲያውኑ ይቋረጥበታል።

፭/ ፈቃዱ የተሰረዘበት ባለሀብት የወሰዳቸውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በሙሉ ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር እና አግባብነት ላላቸው ሌሎች አካላት ይመልሳል።

፮/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፈቃዱን ከሰጠው አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ውጭ በሌላ ማንኛውም አካል ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ አይችልም።

፯/ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የተሰረዘበት የውጭ ባለሀብት ፈቃዱ ከተሰረዘበት ቀን ጨምሮ ከሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ በፊት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማውጣት አይችልም።

፰/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰኑ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀሩም።

**፲፬. ሪፖርት የማድረግ እና የመተባበር ግዴታ**

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣ ማንኛውም ባለሀብት፦

፩/ ስለኢንቨስትመንቱ አፈጻጸም ሂደት በየሦስት ወሩ አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፤

፪/ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ሲጠየቅ ስለሚያካሂደው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት።



4/ The appropriate investment organ shall notify the revocation measure it takes in accordance with this Article to all concerned bodies. Upon revocation of investment permit, the investor shall immediately lose entitlement to all benefits.

5/ An investor whose investment permit is revoked shall return all investment incentives he received to the Ministry of Revenues, the Ethiopian Customs Commission, the Ministry of Finance and other pertinent organs within one month of the revocation.

6/ An investment permit shall only be suspended or revoked by the appropriate investment organ that issued the permit.

7/ A foreign Investor whose investment permit is revoked may not be issued a new investment permit before the lapse of one year since the date of the revocation.

8/ Administrative measures taken under this article shall not affect the right of the Government to bring a criminal action.

**14. Duty to Report and Cooperate**

Any investor who is issued an investment permit shall:

1/ Submit a quarterly progress report on the implementation of his investment project to the appropriate investment organ;

2/ Provide information concerning his investment whenever requested by the appropriate investment organ.

lawyer.et

## ክፍል አምስት

## የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት እና ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር የሚደረጉ የትብብር ስምምነቶች ምዝገባ

### ፲፭. የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ የሚዋዋለውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በኮሚሽኑ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ያልተመዘገበ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በኮሚሽኑ ዘንድ ሕጋዊ እውቅና አይኖረውም፡፡

፫/ ኮሚሽኑ የመዘገበውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ለሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት አስፈጻሚ አካላት እና በግልባጭ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፡፡

### ፲፮.ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳያደርግ የሚያደርገው የትብብር ስምምነት

፩/ ማንኛውም የአገር ውስጥ ባለሀብት ከወጪ ንግድ ጋር በተያያዘ የካፒታል መዋጮ ከማያደርግ የውጭ ድርጅት ጋር የሚፈጽመውን የትብብር ስምምነት በኮሚሽኑ ማስመዝገብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ያልተመዘገበ የትብብር ስምምነት በኮሚሽኑ ዘንድ ሕጋዊ እውቅና አይኖረውም፡፡

፫/ ኮሚሽኑ የመዘገበውን የትብብር ስምምነት ለሚመለከታቸው አስፈጻሚ አካላት እና በግልባጭ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ያሳውቃል፡፡

## PART FIVE

## REGISTRATION OF TECHNOLOGY TRANSFER AND COLLABORATION AGREEMENTS WITH DOMESTIC INVESTORS

### 15. Technology Transfer Agreement

1/ Any investor concluding a technology transfer agreement in relation to his investment shall have the agreement registered with the Commission.

2/ A technology transfer agreement that is not registered in accordance with Sub-article (1) of this Article shall not have legal recognition with the Commission.

3/ The Commission shall notify the relevant Federal Executive Organs and copy the National Bank of Ethiopia the registration of a technology transfer agreement made in accordance with this Article.

### 16. Foreign Enterprise Collaboration Agreement for Export Trade Without Capital Contribution

1/ Any domestic investor who concludes, in respect of export, a collaboration agreement with a foreign enterprise who does not contribute capital shall have the agreement registered with the Commission.

2/ A collaboration agreement that is not registered in accordance with Sub-article (1) of this Article shall not have legal recognition with the Commission.

3/ The Commission shall notify the relevant Federal Executive Organs and copy the National Bank of Ethiopia the registration of a collaboration agreement made in accordance with this Article.

lawyer.et

## ክፍል ስድስት

## የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ ዋስትና እና ጥበቃ፣ እና ማሳለጥ

### ፲፯. የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች

የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለማግኘት ብቁ የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሁም የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ዓይነት እና መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናሉ።

### ፲፰. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን

፩/በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፫፻፺ እስከ አንቀጽ ፫፻፺፫ የተደነገገው ቢኖርም የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ ለኢንቨስትመንት ሥራው የሚያስፈልግ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን ይችላል። ለዚህ ድንጋጌ ዓላማ “የማይንቀሳቀስ ንብረት” መሬትን አይጨምርም።

፪/ በፍትሐብሔር ሕግ ከአንቀጽ ፫፻፺ እስከ አንቀጽ ፫፻፺፫ የተደነገገው ቢኖርም ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ባለቤት የሆነ የውጭ ባለሀብት ወይም እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት የተቆጠረ የውጭ ዜጋ የአንድ መኖሪያ ቤት ባለቤት እንዲሆን ሊፈቀድለት ይችላል። ለዚህ ድንጋጌ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ ዝርዝር ሁኔታዎች በደንብ ይወሰናሉ።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገገው መብት ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በኢንቨስትመንት ሥራ ላይ የተሠማሩ ባለሀብቶችንም ይጨምራል።

## PART SIX

## INVESTMENT INCENTIVES, GUARANTEES AND PROTECTION, AND FACILITATION

### 17.Investment Incentives

Investment areas eligible for investment incentives as well as the type and amount of investment incentives shall be determined by a Regulation to be enacted by the Council of Ministers.

### 18.Ownership of Immovable Property

1/ Notwithstanding the provisions of Articles 390 to 393 of the Civil Code, a foreign investor or a foreign national treated as domestic investor shall have the right to own immovable property necessary for his investment. Immovable property as used in this provision does not include land.

2/ Notwithstanding the provisions of Articles 390 to 393 of the Civil Code, a foreign investor or a foreign national treated as domestic investor who owns large investment may be allowed to own one dwelling house. The detailed conditions necessary for the implementation of this provision shall be specified by a Regulation.

3/The provisions of Sub-articles (1) and (2) of this Article shall be applicable to investors who have invested prior to the adoption of this Proclamation.

lawyer.et

**፲፱. የኢንቨስትመንት ዋስትና እና ጥበቃ**

፩/ መንግሥት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ማንኛውንም ኢንቨስትመንት ለሕዝብ ጥቅም፣ በሕግ አግባብ፣ እና ያለመድልዎ ሊወስድ ይችላል።

፪/ ማንኛውም ኢንቨስትመንት በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የሚወሰድ ከሆነ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ መከፈል አለበት።

**፳.ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ማዛወር**

፩/ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ከሚያካሂደው ኢንቨስትመንት የሚያገኛቸውን የሚከተሉትን ክፍያዎች እና ገቢዎች በወቅቱ ተመን አግባብነት ያለው የአገሪቱ ህግ በሚፈቅደው መሰረት መሠረት በውጭ ምንዛሪ ከኢትዮጵያ ውጭ ማዛወር ይችላል፦

ሀ) ከኢንቨስትመንቱ ያገኘውን ትርፍ እና የትርፍ ድርሻ፤

ለ) ከውጭ አገር ላገኘው ብድር ዋና ገንዘብ እና ወለድ ክፍያ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ መሠረት ካስመዘገበው የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት ካስመዘገበው የትብብር ስምምነት ጋር የተያያዘ ክፍያ፤

ሠ) ለሌላ ባለሀብት አክሲዮን በማስተላለፍ ወይም ድርጅቱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማንኛውም ሌላ ባለሀብት በማዛወር ያገኘው ገንዘብ፤

ረ) ድርጅት ሲሸጥ፣ ካፒታል ሲቀንስ ወይም ፈርሶ ሂሳቡ ሲጣራ የሚገኝ ገቢ፤ እና

ሰ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ-አንቀጽ (፪) መሠረት የሚፈጸም የካሣ ክፍያ።

**19. Investment Guarantees and Protection**

1/The Government may expropriate any investment undertaken under this Proclamation for public interest, in conformity with requirements of the law, and on a non-discriminatory basis.

2/ In case of expropriation of an investment effected pursuant to Sub-article (1) of this Article, adequate compensation corresponding to the prevailing market value shall be paid in advance.

**20.Remittance of Funds**

1/ Any foreign investor shall have the right, in respect of his investment, to remit the following payments and earnings out of Ethiopia in convertible foreign currency at the prevailing exchange rate on the date of transfer:

a) Profits and dividends accruing from his investment;

b) Principal and interest payments on external loans;

c) Payment related to technology transfer agreement registered in accordance with Article 15 of this Proclamation;

d) Payments related to collaboration agreement registered in accordance with Article 16 of this Proclamation;

e) Proceeds from the transfer of shares or conferral of partial or total ownership of an enterprise to another investor;

f) Proceeds from the sale, capital reduction or liquidation of an enterprise; and

g) Compensation paid to an investor pursuant to Sub-article (2) of Article 19 of this Proclamation.

lawyer.et

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም በቅንጅት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ተሳታፊ የሆነ የአገር ውስጥ ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ የሚያገኘውን ገንዘብ ወደ ውጭ ማዛወር አይፈቀድለትም።

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚካሄዱ ኢንቨስትመንቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ቋሚ ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነ የውጭ አገር ዜጎች የሚያገኙትን ደመወዝ አግባብነት ያለው የአገሪቱ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ተመን በውጭ ምንዛሪ ወደ ውጭ አገር መላክ ይችላሉ።

## ፳፩. የውጭ ብድር እና የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልገውን ብድር ከውጭ አገር አበዳሪዎች ተፈጻሚነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ሊወስድ ይችላል።

፪/ ማንኛውም የውጭ ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ ዓላማ የሚውል የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ተፈጻሚነት ባለው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ባንኮች ከፍቶ ማንቀሳቀስ ይችላል።

## ፳፪. የውጭ ዜጎች ቅጥር እና የሥራ ፈቃድ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንቱ አስፈላጊ የሆኑ እና ተገቢ ሙያ ያላቸውን በከፍተኛ ማኔጅመንት፣ በተቆጣጣሪነት፣ በአሰልጣኝነት እና በሌሎች የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የሚሰማሩ የውጭ አገር ዜጎችን መቅጠር ይችላል። ሆኖም የውጭ ዜጎችን መቅጠር የሚችለው ዘርፉ በሚፈልገው ደረጃ ተመሳሳይ ሙያ ወይም ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ማግኘት አለመቻሉ ሲረጋገጥ ነው።

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, a domestic investor investing jointly with a foreign investor shall not be allowed to remit funds earned from the investment out of Ethiopia.

3/ Expats employed for investments carried out pursuant to this Proclamation whose permanent residence is outside of Ethiopia may remit, in accordance with applicable law, salaries accruing from their employment in convertible foreign currency at the prevailing exchange rate on the date of transfer.

## 21. External Loan and Foreign Currency Account

1/ Any investor may acquire external loan for his investment as per the applicable Directive of the National Bank of Ethiopia.

2/ Any investor may operate a foreign currency account in Banks in Ethiopia for the purpose of its investment as per the applicable Directive of the National Bank of Ethiopia.

## 22. Employment of Expats and Work Permits

1/ Any investor may employ duly qualified foreigners necessary for the operation of his investment in positions of higher management, supervision, trainers and other technical professions. However, foreigners may be employed only when it can be ascertained that Ethiopians possessing similar qualification or experience required by the sector are not available.

lawyer.et

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ማንኛውም ባለሀብት ዋና ሥራ አስፈጻሚን፣ ዋና የኦፕሬሽን ኃላፊን እና ዋና የፋይናንስ ኃላፊን ጨምሮ ለኢንቨስትመንቱ የሚያስፈልጉ የውጭ ዜግነት ያላቸው ከፍተኛ የማኔጅመንት አባላትን እንደ አስፈላጊነቱ መቅጠር ይችላል። የከፍተኛ ማኔጅመንት አባላት የሥራ ፈቃድ ሌሎች የውጭ ዜግነት ያላቸው ሠራተኞችን የሚመለከቱ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱ ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት ሳያስፈልግ ይታደሳል።

፫/ የማንኛውም ባለሀብት ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት ተቀጥሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሰራ የውጭ ዜጋ የትዳር አጋር የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የውጭ ዜጎችን የሚቀጥር ባለሀብት ለኢትዮጵያውያን አስፈላጊው ስልጠና እንዲዘጋጅ እና እንዲሰጥ በማድረግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የውጭ አገር ዜጋ ሠራተኞችን እንዲተኩ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፭/ ለውጭ ዜጎች የሥራ ፈቃድ ሊሰጥ የሚችለው በአንድ የሥራ መደብ ለማገልገል እስከ ሦስት አመት ሲሆን እንደ አግባብነቱ ባለሀብቱ በቅድሚያ ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የሌሉ መሆኑን ማረጋገጡን፣ እንዲሁም ተተኪ ኢትዮጵያውያንን በማሰልጠን ረገድ የወሰደውን ተጨባጭ እርምጃ መሠረት በማድረግ በየአመቱ ይታደሳል።

፮/ የውጭ አገር ዜጋ ለተቀጠረበት ሥራ አስፈላጊ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ኮሚሽኑ የሥራ ፈቃዱ እንዳይታደስ ወይም እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል።

፯/ ኮሚሽኑ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከት የአሠራር መመሪያ ያዘጋጃል፣ ተፈጻሚም ያደርጋል፦

2/ Notwithstanding the provision of Sub-article (1) of this Article, an investor may employ foreigners for top management positions, including chief executive officer, chief operation officer and chief finance officer as necessary. The work permit of top management foreign workers shall be renewed without being required to comply with the conditions specified in this Article in respect of other foreign workers.

3/ A work permit may be issued to a cohabiting spouse of any investor and a foreign worker employed pursuant to Sub-article (1) of this Article.

4/ An investor who employs foreigners pursuant to Sub-article (1) of this Article shall be responsible for replacing, within a limited period of time, such foreign workers by Ethiopians by arranging and providing the necessary training.

5/ A work permit for employment in a certain position may be issued for up to three years, and renewed every year subject to verification, as appropriate, that the investor has ascertained the non-availability of Ethiopian workers with similar qualification, and of the concrete measures taken by the investor to train Ethiopian replacements.

6/ Where it is ascertained that a foreign worker is no longer required for the position he is employed, the Commission may decide not to renew or to cancel the work permit.

7/ In collaboration with the Ministry of Trade and Industry and the Ministry of Labour and Social Affairs, the Commission shall prepare and implement a working guideline regulating matters related to:

lawyer.et

ሀ) የውጭ አገር ዜጋ ለሚቀጠርበት የሥራ መደብ የሚኖረውን አስፈላጊነት እና ሙያዊ ተገቢነት፤

ለ) የፈቃድ ዕድሳት ለማከናወን እንዲሟላ የሚጠበቀው የኢትዮጵያውያን ተተኪዎች ስልጠና አፈጻጸም፤

ሐ) በአገር ውስጥ ገበያ ተፈላጊ ችሎታ ያለው ተተኪ የሰው ሀይል መኖር አለመኖሩ የሚረጋገጥበት አግባብ፤ እና

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፯) ከፊደል ተራ (ሀ) እስከ (ሐ) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ወይም በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች የሥራ ፈቃድ የሚሰጥበት፣ ዕድሳት የሚከለከልበት ወይም ፈቃዱ የሚሰረዝበት ሥርዓት።

፰/ ኮሚሽኑ ከንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ባለሀብቶች ለተተኪ ኢትዮጵያውያን ሠራተኞች የስልጠና መርሐግብር በማዘጋጀት የዕውቀት እና የክህሎት ሽግግር እንዲኖር የማድረግ ግዴታቸውን ለመከታተል የሚያስችል የክትትል መመሪያ በማዘጋጀት ይተገብራል።

## ፳፫. የቪዛ አገልግሎት

፩/ ኮሚሽኑ ወይም የውክልና ሥልጣን የተሰጠው የኢንቨስትመንት አካል ከኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ የውጭ አገር ዜጎች እንዲሁም ኢትዮጵያ ውስጥ በኢንቨስትመንት ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ቤተሰቦች (የትዳር አጋር፣ ልጆች እና ወላጆች) ተገቢ ቪዛ እንዲያገኙ ሊያመቻች ይችላል።

፪/ ለኢንቨስትመንት ጉዳዮች ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ከትውልድ ወይም መኖሪያ አገሩ ውጭ የቪዛ ጥያቄ ለሚያቀርብ የውጭ አገር ዜጋ ከኮሚሽኑ ሊሰጥ በሚችል የድጋፍ ደብዳቤ መሠረት ባለበት ሦስተኛ አገር ውስጥ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።

a) Ascertaining the necessity and professional pertinence of expat employees;

b) The execution of training programs involving Ethiopians that replace expat employees;

c) Mechanisms for establishing the availability or otherwise of suitable local workforce having the required expertise; and

d) Procedures governing the issuance, refusal and cancellation of work permits owing to reasons related to matters listed under Sub-article (7) paragraphs (a) to (c) of this Article or other additional grounds.

8/ The Commission, in collaboration with the Ministry of Trade and Industry, shall prepare and implement a guideline regulating the duty of investors to design and provide training programs and to ensure the transfer of skills and knowledge to substitute Ethiopian workers.

## 23. Visa Services

1/ The Commission or a delegated investment organ may facilitate the processing of visa applications of foreigners coming into Ethiopia for investment purposes and that of the families (spouses, children and parents) of investors undertaking investments in Ethiopia.

2/ If a person, intending to enter into Ethiopia for investment purposes, applies for a visa in a country that is not his home country, visa may be issued to him in that third country based on a support letter the Commission may offer.

lawyer.et

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንት ባለቤት ወይም ባለድርሻ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የአምስት ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከናወን ኢንቨስትመንት የሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ የሚሰራ ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ የቦርድ አባል እና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ፣ እንዲሁም የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ሆልዲንግ ኩባንያ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊ ኮሚሽኑ በሚሰጠው ማረጋገጫ መሠረት የሦስት ዓመት የብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ሊሰጠው ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች መሠረት በብዙ ጊዜ መመላለሻ ቪዛ ወደ ኢትዮጵያ የገባ ማናቸውም የውጭ አገር ዜጋ በአንድ ጊዜ የሚኖረው ከፍተኛ የቆይታ ጊዜ ከዘጠና (፺) ቀናት ሊበልጥ አይችልም።

፮/ ለዚህ አንቀጽ ተገቢ አፈጻጸም ኮሚሽኑ ከኢሚግሬሽን፣ ዜግነት እና ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ እና ሌላ አግባብነት ካለው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር ይሰራል።

**፳፬.<u>የአንድ ማዕከል አገልግሎት</u>**

፩/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጣቸው ባለሀብቶች የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፣ አግባብነት ያላቸው ሌሎች አካላትን ያስተባብራል፣ የየዕለት ተግባራቸውን ያቀናጃል።

፪/ የክልል የኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጧቸው ባለሀብቶች አግባብነት ባላቸው የፌደራል እና የክልል ሕጎች መሠረት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣሉ።

3/ An owner or shareholder of an investment undertaken pursuant to this Proclamation may be issued a five-year multiple visa based on confirmation by the Commission.

4/ The General Manager, Board Member and top Management of an Enterprise undertaking an investment pursuant to this Proclamation, and the top management of the parent or holding company of the enterprise may be issued a three-year multiple entry visa based on confirmation by the Commission.

5/ No single stay of any foreigner entering Ethiopia using multiple entry visa issued pursuant to this Article may exceed ninety (90) days.

6/ The Commission shall work in cooperation with the Immigration, Nationality and Vital Events Agency and other appropriate government body for the proper implementation of this Article.

**24.<u>One Stop Service</u>**

1/ The Commission shall provide one-stop services to investors it has issued investment permits pursuant to this Proclamation; it shall coordinate relevant Agencies and synchronize their daily functions.

2/ Regional State investment Organs shall provide one-stop services to investors they issued investment permits in accordance with applicable Federal and Regional State Laws.

lawyer.et

## ክፍል ሰባት
## የአቤቱታ ሥርዓት እና የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት

### ፳፭. አቤቱታ የማቅረብ መብት

፩/ ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር የተያያዘ ቅሬታ ካለው አግባብ ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

፪/ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በተሰጠ የመጨረሻ የአስተዳደር ውሳኔ ላይ በባለሀብት የሚቀርብ አቤቱታ ቀልጣፋ፣ ሚዛናዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይፈታል።

፫/ በዚህ የአዋጁ ክፍል የተደነገገው የአቤቱታ ሥርዓት በኢንቨስትመንት ላይ ለመሰማራት የቀረበ ጥያቄ ላይ አግባብ ባለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔን በመቃወም ለሚቀርብ አቤቱታም ተፈጻሚ ይሆናል።

### ፳፮. የኮሚሽኑ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት በኮሚሽኑ የሚተላለፍ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን በመቃወም ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፪/ የኮሚሽኑ ውሳኔ የጽሑፍ ቅጂ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።

፫/ በኮሚሽኑ በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (፴) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

፬/ ቦርዱ በቀረበለት አቤቱታ ላይ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በዘጠና (፺) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

## PART SEVEN
## GRIEVANCE PROCEDURES AND SETTLEMENT OF INVESTMENT DISPUTES

### 25. Right to Lodge Complaint

1/ Any investor who has grievance in respect of his investment shall have the right to submit a complaint to the appropriate investment organ.

2/ Any complaint submitted by an investor against a final administrative decision shall be resolved using speedy, equitable and efficient procedures.

3/ The grievance procedures provided in this part of the Proclamation shall apply in respect of grievances against a final decision given by the appropriate investment organ on application to engage in investment.

### 26. Grievance Against the Commission's Decisions

1/ Any investor who has grievance against a final administrative decision of the Commission can submit a complaint to the Board.

2/ A written copy of the Commission's decision shall be given to the investor within Seven (7) working days from the date of decision.

3/ Any complaint submitted to the Board against a final administrative decision of the Commission shall be lodged within Thirty (30) working days from the date the investor becomes aware of such decision.

4/ The Board shall give decision on the complaint submitted to it within Ninety (90) working days from the date of submission of the complaint.

lawyer.et

፭/ የቦርዱ ውሳኔ ጽሑፍ ቅጂ ውሳኔው ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ በቦርዱ ጽሕፈት ቤት አማካኝነት ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።

**፳፯. <u>በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚሰጥ ውሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ</u>**

፩/ ማንኛውም ባለሀብት በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን አስመልክቶ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የተላለፈን በኢንቨስትመንቱ ላይ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያደርስ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔን የተመለከተ አቤቱታ ለኮሚሽኑ የማቅረብ መብት አለው።

፪/ የማናቸውም የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ የጽሑፍ ቅጂ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።

፫/ በፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል በተሰጠ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኮሚሽኑ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ባለሀብቱ ውሳኔው መሰጠቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (፴) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

፬/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፩) መሠረት የቀረበ አቤቱታ መፍትሔ እንዲያገኝ አቤቱታ ከቀረበበት የመንግሥት አካል ጋር በመነጋገር አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ (፴) ቀናት ውስጥ የመፍትሔ ሀሳብ በጽሑፍ ያቀርባል።

፭/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) መሠረት ያቀረበው የመፍትሔ ሀሳብ የጽሑፍ ቅጂ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሰባት (፯) የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለሀብቱ ይሰጠዋል።



5/ A written copy of the Board's decision shall be given to the investor by the Secretariat of the Board within Seven (7) working days from the date of decision.

**27. <u>Complaints Against Decisions of Federal Government Executive Bodies</u>**

1/ Any investor undertaking investments pursuant to this Proclamation shall have the right to submit a complaint to the Commission against final decisions of any federal government executive body where such decisions significantly affect the investments.

2/ A written copy of the final decision of any federal Government Executive Body shall be given to the investor within Seven (7) working days from the date of decision.

3/ Any complaint submitted to the Commission against a final administrative decision of a Federal Government Executive Body shall be lodged within Thirty (30) working days from the date the investor becomes aware of the decision.

4/ The Commission shall engage with the government body against whom a complaint is lodged under Sub-article (1) of this Article and propose a recommended solution in writing within Thirty (30) days from the date of submission of the complaint.

5/ A written copy of the Commission's recommended solution proposed under Sub-article (4) of this Article shall be given to the investor within Seven (7) working days from the date the recommended solution is tabled.

lawyer.et

፮/ ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፬) መሠረት ያቀረበውን የመፍትሔ ሀሳብ በመቃወም፣ ወይም የተሰጠው የመፍትሔ ሀሳብ አቤቱታ በቀረበበት የመንግሥት አካል ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ ባለሀብቱ ለቦርዱ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፮) መሠረት ለቦርዱ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ በኮሚሽኑ የቀረበው የመፍትሔ ሀሳብ ለባለሀብቱ በተገለጸ ወይም የመፍትሔ ሀሳቡ አቤቱታ በቀረበበት የመንግሥት አካል ተቀባይነት አለማግኘቱን ባለሀብቱ ባወቀ በሰላሳ (፴) የሥራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት።

፰/ ቦርዱ በቀረበለት አቤቱታ ላይ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በዘጠና (፺) የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

፱/ የቦርዱ ውሳኔ የሚመለከተው ማንኛውም የፌደራል መንግሥት አካል ውሳኔውን የማክበር እና በውሳኔው መሠረት የመፈጸም ግዴታ አለበት።

**፳፰. <u>የኢንቨስትመንት አለመግባባት አፈታት</u>**

፩/ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን በተሰጠው አካል ፍትሕ የማግኘት መብትን ሳይቃረን፤ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በባለሀብት እና በመንግሥት መካከል የሚነሳ ማንኛውም አለመግባባት በውይይት ወይም በድርድር ይፈታል።

፪/ የፌደራል መንግሥት የውጭ ኢንቨስትመንትን በተመለከተ የሚነሱ የኢንቨስትመንት አለመግባባቶች በግልግል ዳኝነት እንዲፈቱ ሊስማማ ይችላል።

፫/ የውጭ ባለሀብት የኢንቨስትመንት አለመግባባትን በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ወይም ለግልግል ዳኝነት ለማቅረብ ከመረጠ ምርጫው የመጨረሻ እና ሌላኛውን ከመጠቀም የሚያግድ ይሆናል።

6/ The investor may file a complaint to the Board against the Commission's recommended solution proposed under Sub-article (4) of this Article, or where the Commission's recommended solution is not accepted by the government body against whom the complaint was submitted.

7/ Any complaint submitted to the Board pursuant to Sub-article (6) of this Article shall be lodged within thirty (30) working days from the date the investor is notified of the recommended solution or from the date the investor learns that the government body against whom the complaint is lodged has rejected the recommended solution.

8/ The Board shall give decision on the complaint submitted to it within Ninety (90) working days from the date of submission of the complaint.

9/ Any Federal Government Body whom a decision of the Board concerns shall have the duty to comply with and Execute in accordance with the decision of the Board.

**28. <u>Settlement of Investment Disputes</u>**

1/ Without prejudice to the right of access to justice through a competent body with judicial power, any dispute between an investor and the Government involving investments effected pursuant to this Proclamation will be resolved through consultation or negotiation.

2/ The Federal Government may agree to resolve investment disputes involving Foreign investments through arbitration.

3/ Where a Foreign investor chooses to submit an investment dispute to a competent body with Judicial Power or arbitration, the choice shall be deemed final to the exclusion of the other.

lawyer.et

## ክፍል ስምንት

## የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

### ፳፱.የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት

የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

፩/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ፤

፪/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

፫/ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ፤ እና

፬/ በክልል ሕጎች የሚወሰኑ የክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት።

### ፴. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

### ፴፩. የቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ቦርዱ፦

ሀ) በዚህ አዋጅ፣ አዋጁን መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦች፣ እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አሰያየም፣ አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለመግዛት በወጡ ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባሮች ይፈጽማል፤

ለ) የዚህን አዋጅ አፈጻጸም እና የኮሚሽኑን ሥራዎች በበላይነት ይቆጣጠራል፣ይከታተላል፤

ሐ) በኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ የፖሊሲ ሀሳብ ያመነጫል፤

መ) እንደ አስፈላጊነቱ ይህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦች እንዲሻሻሉ ሀሳብ ያቀርባል፤

## PART EIGHT

## INVESTMENT ADMINISTRATION ORGANS

### 29.Investment Administration Organs

The Organs of investment administration shall comprise the following:

1/ The Ethiopian Investment Board;

2/ The Ethiopian Investment Commission;

3/ The Federal Government and Regional State Administrations Investment Council; and

4/ Investment administration Organs established pursuant to Regional Laws.

### 30. Ethiopian Investment Board

The Ethiopian Investment Board is hereby re-established under this Proclamation.

### 31. Powers and Duties of the Board

1/ The Board shall:

a) Exercise Powers and Duties specified under this Proclamation, Regulations issued hereunder, and other laws enacted to regulate the designation, operation and supervision of industrial parks;

b) Supervise the implementation of this Proclamation and follow up activities of the Commission;

c) Initiate Policies on matters pertaining to investments;

d) Recommend, as necessary, amendments to this Proclamation and Regulations issued hereunder;

lawyer.et

ሠ) ይህን አዋጅ እና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፣ የመመሪያዎቹን ተፈጻሚነት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

ረ) ኮሚሽኑ ወይም ሌሎች የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካላት በሚሰጡት የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኙ ባለሀብቶች በዚህ አዋጅ በተመለከተው የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት በሚያቀርቡት አቤቱታ ላይ ይወስናል፤

ሰ) ለባለሀብቶች የሚሰጡ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎችን ዓይነት እና መጠን፣ እንደዚሁም በማበረታቻ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው የኢንቨስትመንት መስኮች የሚለዩበትን መመዘኛ በተመለከተ አግባብነት ላለው የመንግሥት አካል በጥናት ላይ የተመረኮዘ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፤

ሸ) ከሚመለከታቸው የመንግሥት እና የግል ዘርፍ አካላት ጋር ተገቢውን ምክክር በማድረግ ከመንግሥት ጋር በቅንጅት የሚካሄዱ፣ ወይም ለአገር ውስጥ ባለሀብት የተከለሉ፣ ወይም ለአገር ውስጥ እና ለውጭ ባለሀብት የቅንጅት ኢንቨስትመንት የተከለሉ የኢንቨስትመንት መስኮች ለውጭ ባለሀብት ክፍት እንዲሆኑ፤ እንዲሁም ክፍት የሆኑ የኢንቨስትመንት መስኮች ለህዝብ ጥቅም ሲባል ከውጭ ባለሀብት ተሳትፎ እንዲከለሉ ይወስናል።

፱/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (፰) ፊደል ተራ (ሸ) መሠረት የሚያሳልፋቸው ማናቸውም ውሳኔዎች ወዲያውኑ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ውሳኔዎቹ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በህትመት ወይም በሌላ መንገድ ለህዝብ ተደራሽ እንዲሆኑ ያደርጋል።

e) Issue Directives necessary for implementation of this Proclamation and Regulations issued hereunder; follow up and oversee the implementation of the Directives;

f) Decide on complaints lodged by investors against final administrative decisions of the Commission or other Federal Government Executive Bodies submitted in accordance with the grievance procedures specified in this Proclamation;

g) Put forward to the pertinent Government Organ an assessment-based recommendation regarding the type and extent of investment incentives to be granted to investments and the criteria for identifying investments eligible for incentives;

h) Decide, in consultation with relevant public and private sector stakeholders, to open to foreign investors those investment areas reserved for joint investment with the government, or to domestic investors, or for joint investment between domestic and foreign investors, as well as restrict foreign investment in areas open to foreign investors where such decision is justified by public interest considerations.

2/ Any decision the Board adopts pursuant to Sub-article (8) paragraph (h) of this Article shall take immediate effect. The decisions of the Board shall be made accessible to the public within one month in published or other forms.

lawyer.et

**፴፪. የቦርዱ አባላት**

፩/ ቦርዱ የሚከተሉት አስራ ሦስት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ……………….......ሰብሳቢ፤

ለ) በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም የመንግሥት ኃላፊ………………………….……ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ) ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከአገልግሎት፣ ከፋይናንስ፣ ከገቢዎች፣ ከግብርና፣ ከኃይል፣ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ዘርፎች አስተዳደር ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ወይም ተዛማጅ የሥራ ኃላፊነት ያላቸው ስምንት የመንግሥት ኃላፊዎች.. አባላት፤

መ) በግሉ የኢንቨስትመንት ዘርፍ የሚሰየሙ ሁለት ተወካዮች..........................................አባል፤ እና

ሠ) የኮሚሽኑ ኮሚሽነር…................አባል እና ጸሀፊ።

፪/ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አካላት ለቦርዱ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

፫/ የግል ኢንቨስትመንት ዘርፍን በመወከል ለቦርዱ አባልነት የሚሰየሙ አባላት፡-

ሀ) በቦርዱ ውሳኔዎች ድምጽ አይሰጡም፤

ለ) ለሁለት አመት የሚያገለግሉ ሆኖ ለተጨማሪ ሁለት አመት ሊሰየሙ ይችላሉ፤

ሐ) ኃላፊነታቸውም ሆነ በቦርዱ ውይይቶች የሚያደርጉት ተሳትፎ በማናቸውም መልኩ ከሚገለጽ የግል ጥቅም ግጭት ነጻ በሆነ መልኩ መወጣት ይኖርባቸዋል፣ የግል ጥቅምን የሚነካ ወይም ማናቸውም የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ጉዳይ ካለ ራሳቸውን ከተሳትፎ ማቀብ ይኖርባቸዋል።

**32. Members of the Board**

1/ The Board shall be constituted of the following Thirteen members:

a) The Prime Minister……………..…Chairperson;

b) A Government official designated by the Prime Minister…………………….......Vice Chairperson;

c) Eight Government Officials having core or related administration mandate over trade, industry,services,finance,revenues,agriculture, energy, and other relevant sectors…Members;

d) Two representatives designated by the private sector ………………………………….Members;

e) The Commission's Commissioner Member and Secretary.

2/ The Chairperson may invite other relevant bodies to meetings of the Board where it is deemed necessary.

3/ Private sector representatives designated to be members of the Board:

a) Shall not vote in the Board's decisions;

b) Shall serve a term of two years and may be reappointed for one more term;

c) Shall participate in the Board's proceedings and discharge their responsibility free from any direct or indirect situations creating conflict of interest; they shall recuse themselves from deliberations of the Board in respect of matters which involve their personal interest or give rise any form of conflict of interest;

lawyer.et

፬/ ቦርዱ አጠቃላይ አሠራሩ የሚመራበት፣ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱበት፣ የሚያያቸው ጉዳዮች የሚቀርቡበት እና ውሳኔዎች የሚሰጡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

፭/ ኮሚሽኑ የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል። የቦርዱ ጽህፈት ቤት የራሱን የሰው ሀይል ያደራጃል።

## ፴፫. የቦርዱ ስብሰባዎች

፩/ ቦርዱ በየሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የቦርዱ አባላት በማንኛውም ስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።

፫/ የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም የተሰጠ ድምጽ ዕኩል የሆነ እንደሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ ያልፋል።

## ፴፬. የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴ

ቦርዱ እንደ አስፈላጊነቱ የኢንቨስትመንት አማካሪ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ አባላቱን እና ሰብሳቢዎቻቸውን ይሰይማል።

## ፴፭. የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መስሪያ ቤት፤ ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።

## ፴፮. ዋና መስሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ውስጥ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ቦታ ቅርንጫፍ ወይም ተጠሪ ጽህፈት ቤት ሊኖረው ይችላል።

4/ The Board shall adopt a Directive determining the procedure for its overall working, the conduct of meetings, the submission of matters it considers, and the rendering of decisions.

5/ The Commission shall serve as Secretariat of the Board; the Secretariat shall organize its own staff.

## 33. Meetings of the Board

1/ The Board shall meet once every quarter but may meet additionally as it deems it necessary.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Board are present at any meeting.

3/ Decisions of the Board shall pass by majority vote; the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

## 34. Investment Advisory Committee

The Board may, as necessary, establish Investment Advisory Committees, define their Mandates and designate their Membership and Chairpersons.

## 35. Ethiopian Investment Commission

The Ethiopian Investment Commission is hereby reestablished as an autonomous Federal Government Agency having its own legal personality and being accountable to the Prime Minister.

## 36. Head Office

The Commission shall have its head office in Addis Ababa and may, as necessary, have branch or liaison office elsewhere.

lawyer.et

**፴፯. <u>ዓላማ</u>**

የኮሚሽኑ ዓላማ ለኢንቨስትመንት ምቹ የሆነ ከባቢያዊ ሁኔታ መፍጠር፣ ኢንቨስትመንትን መሳብ እና ማቆየት፣ እና ግልጽ እና ቀልጣፋ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ ነው።

**፴፰. <u>የኮሚሽኑ ሥልጣን እና ተግባር</u>**

ኮሚሽኑ፡-

፩/ በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ መሠረት አድርገው በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮች አስተዳደር እና ቁጥጥርን ለመግዛት በወጡ ሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሥልጣን እና ተግባሮች ሥራ ላይ ያውላል፤

፪/ የኢንቨስትመንት ጉዳዮችን በተመለከተ በማዕከልነት በማገልገል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ይመራል፣ ያበረታታል፣ ያስተባብራል፣ ያስፋፋል፤

፫/ ምቹ እና ተወዳዳሪ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ የሚወሰዱ የፖሊሲ እና የአፈጻጸም ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ ኢንቨስትመንት የማስተዋወቅ ሥራዎችን ይመራል፣ በኢንቨስትመንት ተሳትፎ ሊያደርጉ የሚችሉ ተፈላጊ ባለሀብቶችን ዝርዝር ያደራጃል፣ እንዲሁም የተመረጡ ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችሉ ሥራዎችን ያከናውናል፤

፭/ አገሪቱ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ መሆኗን የሚያሳዩ የአዲስ ገጽታ ማቋቋም እና ግንባታ ሥራዎችን ይሰራል፣ በየዘርፉ ተነጻጻሪ የውድድር አቅሞችን እና የንግድ ሥራ ስኬትን የሚያመላክቱ መረጃዎችን የያዙ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለይቶ ያደራጃል፣ የዘርፍ ፕሮፋይሎችን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ ጽሑፎችን ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣ ዓውደ-ርዕዮችን፣ እና ሴሚናሮችን በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ያካሂዳል፣ በተዘጋጁ ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ላይ ይሳተፋል፣ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

**37.<u>Objective</u>**

The Objectives of the Commission shall be to establish a conducive investment climate, attract and retain investments, and implement a transparent and efficient investment administration system.

**38.<u>Powers and Duties of the Commission</u>**

The Commission shall:

1/ Exercise Powers and Duties specified under this Proclamation, Regulations and Directives issued hereunder, as well as other laws enacted to administer and regulate industrial parks;

2/ Serve as nucleus for matters of investment and lead, promote, coordinate and enhance activities thereon;

3/ Initiate policy and implementation measures required to create a conducive and competitive investment climate, and follow up execution of same upon approval;

4/ Lead investment promotion activities, compile a list of potential investors, and implement targeted investor recruitment work;

5/ Rebrand and build the country's image as a preferred investment location; identify and compile investment opportunities in each sector indicating investment value propositions and business success, and prepare profile and promotional documents on each sector and disseminate same; organize workshops and seminars locally or abroad; and, participate in similar events and conduct trainings;

lawyer.et

፮/ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት እድል መግለጫዎችን በማዘጋጀት ያስተዋውቃል፣ ሲጠየቅም በቅንጅት ለሚደረግ ኢንቨስትመንት ተሳታፊዎችን የማገናኘት አገልግሎት ይሰጣል፤

፯/ በአገራዊ የኢንቨስትመንት እድሎችን የማስተዋወቅ እንቅስቃሴ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ማስተዋወቅ አንዱ እና ወሳኙ ሥራው አድርጎ ይንቀሳቀሳል፤

፰/ በመንግሥት ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኖሩ ምቹ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ከማስተዋወቅ፣ ባለሀብቶችን ከመሳብ እና ከመመልመል ጋር በተያያዘ በማዕከልነት የሀብት ብክነትን የሚቀንስ ሥርዓት በማደራጀት የተቀናጀ፣ ተደራሽ እና ትክክለኛ መረጃ ለባለሀብቶች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያቀርባል፤

፱/ የውጭ ኢንቨስትመንቶች ሊመጡ ከሚችሉባቸው አገሮች ጋር አገሪቱ የምታደርጋቸውን የሁለትዮሽ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ እና ጥበቃ ስምምነቶች ተፈጻሚነት ባለው የዓለምአቀፍ ስምምነቶች መዋዋያ እና ማጽደቂያ ሕግ ሥርዓት መሠረት ይደራደራል፣ ይፈርማል፤

፲/ በኮሚሽኑ፣ በባለሀብቶች እና እና በሌሎች መንግሥታዊ አካላት መካከል ወቅታዊ እና ትክክለኛ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል የመረጃ መለዋወጫ ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል፤

፲፩/ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት በባለሀብቶች፣ በመንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች፣ በክልል መስተዳድሮች እና በሌሎች ኢንቨስትመንትን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው አካላት መካከል ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል፣ ያስተባብራል፤

6/ Promote existing investment opportunities by preparing materials on same, and provide, upon request, link-up services for participants of joint investment;

7/ Make industrial parks promotion one of its core undertakings within the national investment promotion work;

8/ Establish as a core agency a cost-effective system for and to provide a coordinated, accessible and accurate information to investors and other concerned bodies with the purpose of promoting investment opportunities in government-owned industrial parks and attracting and recruiting investors;

9/ Negotiate and sign bilateral investment promotion and protection treaties with countries that can be sources of outward foreign investment in accordance with the procedure under the applicable law on international treaty making and ratification;

10/ Cause the establishment of an information exchange system that enables current and accurate information flow between the Commission, investors and other government agencies;

11/ Facilitate liaison and effect coordination between investors, government agencies, regions and other organs concerned with investment with a view to enhancing investment;

lawyer.et

፲፪/ ማንኛቸውንም ኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያጠናቅራል፣ ወቅታዊ ያደርጋል፣ ይተነትናል፣ ያሰራጫል፤

፲፫/ በተሰጠው የሥልጣን ክልል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፤ እንዲሁም የውጭ ባለሀብቶች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ካፒታል ይመዘግባል፤

፲፬/ ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን ይመዘግባል፤

፲፭/ የውጭ ድርጅት የካፒታል መዋጮ ሳያደርግ ከውጭ ንግድ ጋር በተያያዘ ከአገር ውስጥ ባለሀብት ጋር የሚያደርገውን የትብብር ስምምነት ይመዘግባል፤

፲፮/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሰጣቸውን ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ደረጃ እና አፈጻጸም ይከታተላል፣ የኢንቨስትመንት ፈቃዱ የያዛቸው ሁኔታዎች መከበራቸውን፣ ማበረታቻዎች ለታለመላቸው ዓላማ መዋላቸውን እንዲሁም ብሔራዊ የኢንቨስትመንት ዓላማዎች መሟላታቸውን ይቆጣጠራል፤

፲፯/ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፤

፲፰/ የድህረ-ኢንቨስትመንት የድጋፍ እና ክትትል ሥራን ለዚህ ዓላማ ከተቋቋሙ አካላት ጋር በቅንጅት ያከናውናል፤

፲፱/ የክልል አግባብ ያላቸው ኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶችን ለማጠናከር የሚረዱ የምክር እና የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል፣ የጋራ የምክክር መድረኮችን ያዘጋጃል፤

፳/ ባለሀብቶች በዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ያደርጋል፤

12/ Collect, compile, update, analyze and disseminate any investment-related information;

13/ Issue, renew and cancel investment permits within its jurisdiction and register capital brought into the country by foreign investors;

14/ Register technology transfer agreements related to investments;

15/ Register a collaboration agreement for export trade without capital contribution between a domestic investor and foreign enterprise;

16/ Monitor the progress and implementation of investment projects for which it has issued permits; ensure that the terms of the investment permit are complied with, that incentives granted to investors are used for the intended purposes, and that national investment objectives are met;

17/ Provide and coordinate one-stop services;

18/ Carry out post-investment support and monitoring services in collaboration with bodies established for the purpose;

19/ Extend advisory and technical support services to strengthen appropriate investment organs of Regions, and organize joint consultation forums;

20/ Raise investors' awareness on the contents of this Proclamation as well as Regulations and Directives issued hereunder;

lawyer.et

፳፩/ ከባለሀብቶች እና ማህበሮቻቸው ጋር መደበኛ እና በሥርዓት የተዋቀረ የመንግሥት እና የግል ዘርፍ ምክክሮችን ያካሂዳል፣ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲፈቱ ያደርጋል፤

፳፪/ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን መመሪያዎች እና ውሳኔዎች ይፈጽማል፤ በሚመለከታቸው ሌሎች አካላት መተግበራቸውንም ይከታተላል፤

፳፫/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፳፬/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

፳፭/ በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ከሚመለከታቸው የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር አካላት ጋር በቅንጅት ያከናውናል።

## ፴፱. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፦

፩/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ኮሚሽነር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፤ እና

፪/ ለሥራው የሚያስፈልጉ ሠራተኞች ይኖሩታል።

## ፵.<u>የኮሚሽነር ሥልጣን እና ተግባር</u>

ኮሚሽነሩ፦

፩/ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኮሚሽኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፤

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፰ የተመለከቱትን የኮሚሽኑን ሥልጣን እና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

21/ Hold regular and structured public-private dialogue with investors and their associations, cause investment bottlenecks to be resolved in collaboration with appropriate Government Organs;

22/ Implement directives and decisions of the Board, and follow up their implementation by other relevant bodies;

23/ Own property, enter into contract, and sue and be sued in its own name;

24/ Carry out other functions pertinent for proper implementation of its objectives;

25/ Carry out the functions entrusted to it herein in coordination with other Federal Government and Regional State Administration Bodies.

## 39. <u>Organization of the Commission</u>

The Commission shall have:

1/ A Commissioner and Deputy Commissioners to be appointed by the Prime Minister; and

2/ The necessary staff.

## 40. <u>Powers and Duties of the Commissioner</u>

The Commissioner shall:

1/ Be the Chief Executive Officer of the Commission and shall, subject to general instructions given by the Board, direct and administer activities of the Commission;

2/ Exercise Powers and Duties of the Commission specified under Article 38 of this Proclamation;

lawyer.et

፫/ የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል የሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

፬/ ከተለያዩ የልማት አጋራት እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚፈጸሙ የተቋማዊ አቅም ግንባታ ትብብር ሁኔታዎችን ይወስናል፤

፭/ በተሰጠው ሥልጣን ማዕቀፍ ይህን አዋጅ እና አዋጁን መሠረት አድርገው የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ያወጣል፤

፮/ የኮሚሽኑን የሥራ መርሐግብር እና በጀት አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፯/ ለኮሚሽኑ በተፈቀደው በጀት እና የሥራ መርሐግብር መሠረት ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

፰/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኮሚሽኑን ይወክላል፤

፱/ የኮሚሽኑን የሥራ አፈጻጸም እና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያቀርባል፤

፲/ ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣን እና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽኑ ሌሎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች በውክልና ይሰጣል።

## ፵፩ .የምክትል ኮሚሽነር ሥልጣን እና ተግባር

፩/ ምክትል ኮሚሽነሩ፦

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት እና በማስተባበር ኮሚሽነሩን ይረዳል፤

ለ) በኮሚሽኑ መዋቅር መሠረት የሥራ ክፍፍል በማድረግ ከኮሚሽኑ ዘርፎች ከፊሉን ይከታተላል፤

3/ Employ, administer, and dismiss employees of the Commission in accordance with the Federal Civil Servants' Law;

4/ Determine conditions of institutional capacity building agreements concluded with various development partners and pertinent stakeholders;

5/ Adopt Directives regulating matters falling within the scope of its Powers and required for the implementation of this Proclamation and Regulations adopted hereunder;

6/ Prepare and submit work program and budget of the Commission to Office of the Prime Minister, and implement the same upon approval;

7/ Effect payments in accordance with the approved budget and work program of the Commission;

8/ Represent the Commission in its dealings with third parties;

9/ Prepare and submit performance and financial reports of the Commission to Office of the Prime Minister;

10/ Delegate part of his powers and duties to other officers and staff of the Commission as necessary for the efficient performance of the Commission's activities.

## 41. Powers and Duties of the Deputy Commissioner

1/ The Deputy Commissioner shall:

a) Assist the Commissioner in the directing, administering and organizing the functions of the Commission;

b) Oversee parts of the Commission's departments by assigning functions in accordance with the structure of the Commission;

lawyer.et

ሐ) ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ እሱን ተክቶ ይሰራል፤

መ) ከኮሚሽነሩ ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

፪/ምክትል ኮሚሽነሩ ተጠሪነቱ ለኮሚሽነሩ ይሆናል።

**፵፪. <u>በጀት</u>**

የኮሚሽኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

**፵፫.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>**

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉ እና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የኮሚሽኑ የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ-ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናው ኦዲተር በሚሰይመው ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራሉ።

**፵፬. <u>የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት ጉባዔ መቋቋም</u>**

የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች የኢንቨስትመንት አስተዳደርን በተመለከተ በትብብር እና በቅንጅት የሚሰሩበት ጉባዔ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

**፵፭.<u>የጉባዔው ሥልጣን እና ተግባር</u>**

ጉባዔው፡-

፩/ የተቃለለ እና የተቀናጀ የኢንቨስትመንት አሠራር ለማስፈን በአገራዊ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ጉዳዮች በፌደራል መንግሥት እና በክልል መስተዳድሮች መካከል የሚኖረውን ሁሉን-አቀፍ የጎንዮሽ ግንኙነት እና ቅንጅት በበላይነት ይመራል፤

c) Act on behalf of the Commissioner in his absence;

d) Perform such other duties as may be specifically entrusted to him by the Commissioner.

2/ The Deputy Commissioner shall be accountable to the Commissioner.

**42. <u>Budget</u>**

The Commission's budget shall be allocated by the Government.

**43.<u>Books of Account</u>**

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of account.

2/ The books of account and financial documents of the Commission shall be audited annually by the Federal Auditor General or another Auditor designated by the Federal Auditor General.

**44.<u>Establishment of the Federal Government and Regional State Administrations Investment Council</u>**

A Council for the cooperative and coordinated administration of investment between the Federal Government and Regional State Administrations is established by this Proclamation.

**45.<u>Powers and Duties of the Council</u>**

The Council shall:

1/ Direct and oversee all aspects of the horizontal relationship and coordination between the Federal Government and Regional State Administrations on matters relating to investment administration with the objective of establishing simplified and synchronized investment system;

lawyer.et

፪/ በኢንቨስትመንት አስተዳደር የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮች በሚኖራቸው ሥልጣን እና ኃላፊነት ዙሪያ በሚነሱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል ወይም የመፍትሔ ሀሳብ ይሰጣል፣ ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦችም አግባብነት ላለው ተቋም እንዲተላለፉ በማድረግ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

፫/ የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድሮችን በሚያገናኙ የሥራ ሂደቶች የኢንቨስትመንት አገልግሎት አፈጻጸምን ለመገምገም የሚያስችል የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፣ የኢንቨስትመንት አገልግሎት አፈጻጸም እንቅፋት የሚሆኑ ጉዳዮችን መከላከያ እና ማስተካከያ ሥርዓት ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚካሄድ ኢንቨስትመንትን መሠረት በማድረግ ባለሀብቶች የመሬት አቅርቦትን ጨምሮ ከክልል የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት የሚያገኙትን የቅድመ-ኢንቨስትመንት እና ድህረ-ኢንቨስትመንት አገልግሎት አሰጣጥን በማስመልከት በሚነሱ መሠረታዊ ቅሬታዎች ወይም ጉልህ አለመግባባቶች ላይ ውሳኔ ወይም የመፍትሔ ሀሳብ ይሰጣል።

**፵፮. የጉባዔው አባላት**

ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

፩/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖሩበት ጊዜ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ……………………………………….ሰብሳቢ፤

፪/ የሁሉም ክልሎች ርዕሰ-መስተዳድሮች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባዎች…...........................አባል፤

2/ Deliberate and decide on or put forth a recommended solution for all matters ensuing pertaining to the exercise of powers and functions of the Federal Government and Regional State Administrations involving investment administration, and ensure that such decisions or recommended solutions are conveyed to the relevant institution and complied with;

3/ Establish an oversight system that enables evaluation of workflow between the Federal Government and Regional State Administrations in respect of implementation of investment services; put into action a system to prevent and resolve hindrances to the provision of investment services;

4/ Render decisions or put forth recommended solutions on fundamental grievances or significant misunderstandings submitted by investors regarding the provision of pre-investment and post-investment services, including the allocation of land, by regional state investment administration bodies with respect to investments effected under this Proclamation.

**46. Members of the Council**

The Council shall have the following members:

1/ The Prime Minister, or in his absence, the Deputy PrimeMinister………………………..Chairperson;

2/ Presidents of all Regions and Mayors of the Addis Ababa City Administration and Dire Dawa City Administration………………………..…Members;

lawyer.et

፫/ ኮሚሽነሩ፣ የሁሉም ክልሎች እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ኃላፊዎች...............................................አባል፤ እና

፬/ እንደ አስፈላጊነቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ አባላት።

## ፵፯. <u>የጉባዔው ስብሰባዎች</u>

፩/ ጉባዔው በየስድስት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም አስቸኳይ ጉዳይ ሲኖር በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ የጉባዔው አባላት በስብሰባ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል።

፫/ ጉባዔው በጉዳዮች ላይ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውይይት በማካሄድ ውሳኔ ያሳልፋል ወይም የመፍትሔ ሀሳቦችን ያጸድቃል።

፬/ ማናቸውም የፌደራል መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድር አካል የጉባዔውን ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦች ይፈጽማል።

## ፵፰. <u>የጉባዔው ጽህፈት ቤት</u>

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የጉባዔው ጽህፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል።

## ፵፱. <u>የጉባዔው ተቋማዊ አሠራር</u>

ጉባዔው አጠቃላይ አሠራሩ የሚመራበት፣ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱበት፣ የሚያያቸው ጉዳዮች የሚቀርቡበት እና ውሳኔዎች ወይም የመፍትሔ ሀሳቦች የሚሰጡበትን ሥርዓት የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

3/ The Commissioner, heads of the appropriate investment organs of all Regions and Addis Ababa City Administration and Dire Dawa City Administration…………………….……Members;

4/ Other members designated by the Prime Minister as necessary.

## 47. <u>Meetings of the Council</u>

1/The Council shall meet once every six months but may meet additionally where it is deemed necessary or a matter requiring immediate attention arises.

2/ There shall be quorum where more than half of the members of the Council are present at any meeting.

3/ In relation to matters submitted to it, the Council shall pass decisions or adopt recommended solutions based on evidence and informed discussions.

4/ Any Federal Government or Regional State Administration body shall execute the decisions or recommended solutions of the Council.

## 48. <u>Secretariat</u>

The Office of the Prime Minister shall serve as Secretariat of the Council.

## 49. <u>Institutional Working of the Council</u>

The Board shall adopt a Directive determining the procedure for its overall working, the conduct of meetings, the submission of matters it considers, and the rendering of decisions or recommended solutions.

lawyer.et

**፶. <u>ከክልል የኢንቨስትመንት አስተዳደር አካላት ጋር የሚኖር ቅንጅት</u>**

፩/ ወጥ የሆነ፣ የተቀናጀ እና የተቀላጠፈ ብሔራዊ የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥርዓትን ለመመሥረት ኮሚሽኑ በክልል ሕጎች ከሚመሠረቱ የኢንቨስትመንት አስተዳደር እና ባለድርሻ አካላት ጋር በጥብቅ ትብብር ይሰራል።

፪/ ለዚህ ዓላማ አፈጻጸም ኮሚሽኑ ከክልሎች ጋር የሚኖረውን ሁሉን-አቀፍ የአሠራር ግንኙነት የሚመራ መመሪያ አግባብ ካላቸው የክልል የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ ያዘጋጃል።

፫/ ተጨባጭ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ፣ የአስተዳደር ሥራዎችን ለማቀናጀት እና በሂደቱም የክልሎችን ተሳትፎ ለማጠናከር፣ እንዲሁም ከኮሚሽኑ የኢንቨስመንት ፈቃድ ያገኙ ባለሀብቶች በክልል የሚያገኙትን የቅድመ- እና የድህረ-ኢንቨስትመንት አገልግሎት የተሳለጠ ለማድረግ እና የሚያጋጥሙ ማነቆዎችን ለማቃለል እንዲቻል በኮሚሽኑ ተቋማዊ መዋቅር ውስጥ ቋሚ የክልል ኢንቨስትመንት አስተዳደር ዴስኮች ይቋቋማሉ።

**50. <u>Coordination with Regional State Investment Administration Organs</u>**

1/The Commission shall work in close cooperation with Regional State Investment Administration Organs and other Stakeholders with a view to creating a uniform, coordinated and efficient national investment administration system.

2/ For such purposes, the Commission shall engage with appropriate investment organs of Regions to jointly develop a comprehensive guideline regulating all aspects of mutual work relationships.

3/ Standing Regional State Investment Desks shall be established within the functional structures of the Commission which shall work on co-promoting concrete investment opportunities of regions, coordinate common administrative works and augment the Regions' participation in investment administration; they shall also facilitate the efficient provision of pre- and post-investment services and resolve investment bottlenecks encountered by investors issued investment permits by the Commission.

**፶፩. <u>የኢንቨስትመንት መሬት አቅርቦትን በተመለከተ የሚፈጸሙ አሠራሮች</u>**

፩/ ክልሎች አግባብነት ባላቸው የፌደራል የመሬት አስተዳደር ሕጎች የተሰጣቸውን ሥልጣን መሠረት በማድረግ ለማምረቻ ዘርፍ፣ ለእርሻ እና ሌሎች የኢንቨስትመንት መስኮች የሚውሉ የመሬት አቅርቦት ጥያቄዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ያስተናግዳሉ፣ ለዚህ የሚሆን ግልጽ እና ተገማች ሥርዓትም ሊዘረጉ ይችላሉ።

**51. <u>Procedures Followed with Respect to the Provision of Investment Land</u>**

1/ In pursuance of Powers granted to them under the pertinent Federal Land Administration Laws, Regions shall handle land requests for investments in the manufacturing, agriculture, and other sectors in an efficient manner, and shall establish a transparent and predictable system for the handling of such requests.

lawyer.et

፪/ ክልሎች ለኢንቨስትመንት ሥራ የሚውል መሬትን አስቀድሞ በመለየት፣ በመመደብ እና በአንድ ተጠሪ ክልላዊ አካል ሥር በማደራጀት መረጃዎቹን አግባብነት ላለው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ያስተላልፋሉ።

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚከናወን ኢንቨስትመንት የተሰጠ ፈቃድን መሠረት በማድረግ ለክልል አካል የሚቀርቡ የመሬት አቅርቦት ጥያቄዎች በተሳለጠ ሁኔታ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ኮሚሽኑ ከክልል መስተዳድሮች እና አግባብ ካላቸው የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤቶች ጋር በመቀናጀት የማስተባበር እና የክትትል ሥራዎችን ያከናውናል።

፬/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በተሰጠው ባለሀብት ለኢንቨስትመንት ሥራ የሚውል መሬት አቅርቦት ጥያቄ የቀረበለት የክልል መስተዳድር አካል ለማምረቻ ዘርፍ የሚውለውን መሬት በስልሳ (፷) ቀናት ውስጥ፤ ለሌሎች ዘርፎች የሚውል መሬትን አስመልክቶ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ ደግሞ በዘጠና (፺) ቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ የሚያስችል ልዩ አሠራር ክልሎች ሊዘረጉ ይችላሉ።

**፶፪. <u>የኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎችን ማቅረብ</u>**

፩/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣን እና ተግባር በአግባቡ መወጣት እንዲችል አግባብነት ያላቸው የፌደራል መንግሥት እና የክልል መስተዳድር አካላት ለተለያዩ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚውሉ መሬቶችን፣ የመሬት አጠቃቀም ፕሮፋይል እና ሌሎች አስፈላጊ፣ የተሟሉ እና ወቅታዊ ኢንቨስትመንት-ነክ መረጃዎችን ለኮሚሽኑ ማስተላለፍ አለባቸው።

2/ Regions shall identify and classify land to be used for investment projects, organize such land centrally under one Regional State Administration body and transfer the information to the appropriate investment organs.

3/ With respect to land provision requests submitted to Regional State Bodies in respect of an investment undertaken based on an investment permit issued pursuant to this Proclamation, the Commission shall coordinate with Regional State Administrations and appropriate investment organs to facilitate and follow through the efficient handling of such requests.

4/ Regions may establish a Special Procedure requiring the pertinent Regional State Body to respond to land allocation request made by an investor holding investment permit issued under this Proclamation within sixty (60) days where the investment is in the manufacturing sectors, and within Ninety (90) days where the investment is in other sectors.

**52. <u>Provision of Investment-Related Information</u>**

1/Concerned Federal Government and Regional State Administration Bodies shall transfer information regarding land allocated for various investment projects, land use profile, and other relevant, complete and updated investment-related information to the Commission in order to enable the Commission discharge its Powers and Duties under this Proclamation.

lawyer.et

፪/ እያንዳንዱ አግባብ ያለው የክልል ኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት ስለክልሉ የሀብት ክምችት እና የኢንቨስትመንት ዕድል የተጠናቀረ መረጃ፣ እንዲሁም ስለክልሉ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የተዘጋጁ ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለኮሚሽኑ ያስተላልፋል።

## ክፍል ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፶፫. የኢንዱስትሪ ፓርኮች

በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የተመለከቱ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የኢንቨስትመንት ሕጎች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

### ፶፬. ሌሎች ሕጎችን የማክበር እና ዘላቂ የማህበራዊ እና የአካባቢ ጉዳዮች ግዴታ

፩/ ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ተግባሩን የአገሪቱን ሕጎች በማክበር ያከናውናል።

፪/ ማንኛውም ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቱን ተግባራዊ ሲያደርግ የአካባቢ ጥበቃ ደረጃዎች እና የማህበራዊ አካታችነት ዓላማዎችን ጨምሮ ለዘላቂ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ እሴቶች ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስ አለበት።

### ፶፭. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል።

፪/ ቦርዱ፣ ኮሚሽኑ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለሥልጣን፣ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን፣ እና የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ይህን አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ።

2/ The appropriate investment organ of each Region shall transmit to the Commission updated information on resource potentials, investment opportunities and investment activities conducted in the Region.

## PART NINE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 53. Industrial Parks

Unless otherwise indicated in this Proclamation, other relevant Investment Laws concerning Industrial Parks shall remain in force.

### 54. Duty to Observe Other Laws and Social and Environmental Sustainability Values

1/ All investors shall carry out their investment activities in compliance with the Laws of the country.

2/ All investors shall give due regard to social and environmental sustainability values including environmental protection standards and social inclusion objectives in carrying out their investment projects.

### 55. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers shall issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Board, the Commission, the Ethiopian Civil Aviation Authority, the Energy Authority, and the Ethiopian Communications Authority may issue Directives for the implementation of Regulations enacted pursuant to this Proclamation.

lawyer.et

**፶፮. <u>የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>**

፩/የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድን እና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲፫/፪ሺ፮ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

፪/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፲፫/፪ሺ፮ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን መብቶች እና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ለተቋቋመው ኮሚሽን ተላልፈዋል።

፫/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፶፯. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ የተደነገገው ቢኖርም ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶችን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር ፯፻፷፱/፪ሺ፬ (እንደተሻሻለ) እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦች እና መመሪያዎች መሠረት የተሰጡ መብቶች እና ጥቅሞች ተፈጻሚነት ይቀጥላል።

**56. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>**

1/ The Investment Proclamation No.769/2012 (as amended) and the Ethiopian Investment Board and Ethiopian Investment Commission Establishment Council of Ministers Regulation No. 313/2014 are hereby repealed.

2/ The Rights and Obligations of the Ethiopian Investment Commission established by Council of Ministers Regulation No. 313/2014 are transferred to the Commission reestablished by this Proclamation.

3/ No law or customary practice shall have effect with respect to matters provided for in this law so far as it is inconsistent with this Proclamation.

**57. <u>Transitory Provision</u>**

Notwithstanding the Provisions of Article 56 of this Proclamation, Rights and entitlements bestowed pursuant to Investment Proclamation No.769/2012 (as amended) and Regulations and Directives issued there under shall remain applicable in respect of investments approved prior to the coming into force of this Proclamation.

lawyer.et

**፶፰. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**58. Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazettee.

**አዲስ አበባ መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሣህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**Done at Addis Ababa, On the 2nd Day of April 2020.**

**SHALEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

**REPUBLIC OF ETHIOPIA**

lawyer.et